# ኢሕአዴግ ለምን ብርቱካን ሚደቅሳን ይፈታል ?

ግርማ ካሳ
(muziky68@yahoo.com)

ጥቅምት 3 ቀን 2002

ምርጫዉን በተመለከተ የተለያዩ አስተያየቶች እየተሰጡ ነዉ። በተለይም የአንድነት ፓርቲ ዋና ጸሃፊ አቶ አሥራት ጣሴ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ዙሪያ የሰጡት ቃለ መጠይቅ ትንሽ እሳትን እንደለኮሰ እያየን ነዉ። (ኢንጂነር ግዛቸዉ እሳቱን ለማጥፋት ቢሞክሩም)

በዉጭ አገር ካሉ የአንድነት ደጋፊዎች እንዲሁም በተለያዩ የፓልቶክ ክፍል ያሉ ኢትዮጵያዉያን የሚሰጡት አስተያየቶችና በየድህረ ገጾች የሚጻፉ ጽሁፎች የሚያመለክቱት ነገር ቢኖር፣ ወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳ በታሰረችበት ሁኔታ ወደ ምርጫዉ መግባት ትልቅ ተቃዉሞን ሊያስነሳ እንደሚችል ነዉ።

በአገር ቤትም ተመሳሳይ ሁኔታ ያለ ይመስላል። የአዉራምባ ታይምሱ አቶ ዳዊት ከበደ ላቀረበላቸዉ ጥያቄ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ሲመልሱ «ብርቱካን የአንድነት ሊቀመንበር ነች። መሪያችን ነች። ስለዚህ እሷን ከሌሎች ሰዎች ጋር አናያትም። በመሪነቷ፣ በእናትነቷና በመስራችነቷ ለብቻዋ ነዉ የምንመለከታት። እና እርሷን እሥር ቤት አስገብተን ምርጫ ሊኖር አይችለም የሚል አስተሳሰብ እና አቋም ነዉ ያለን» ነበር ያሉት።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የታሰረችዉ ለአንድ አላማ ነዉ። እርሱም በኢትዮጵያ ሕግ የበላይ ሆኖ፣ የዜጎች መብት ተከበሮ፣ በነጻነቷና በአንድነቷ ታፍራና ተከብራ የምትኖር አንዲት የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመመስረት ነዉ። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ከሁሉም በላይ የርሷ መታሰር ሳይሆን የሚያሳስባት፣ የታሰረችበት ዓላማ ከግቡ የመድረሱና ያለመድረሱ ጉዳይ ነዉ እንጂ። ይህማ ባይሆን ኖሮ መጀመሪያዉኑ እዉነትን ሰርዛ፣ ያልሆነዉን ሆነ ብላ አገዛዙ የጠየቃትን አሚልታ አለመታሰር ትችል ነበር።

እስቲ ትንሽ አይምሮዋችንን እንዲጫር አንዳንድ ጥያቄዎችን ላቅርብ። እርስ በርስ ሳንስማማና አንድነት ሳይኖረን፣ ዝም ብለን ወደ ምርጫዉ ብንገባ ምን የምናመጣዉ ለዉጥ አለ ? በእዉኑ አቶ አሥራት ጣሴ እንዳሉት አሁን ባለዉ አሳዛኝ የፖለቲካ ሁኔታ ምርጫዉን አሸንፈን ብርቱካን ሚደቅሳና ማስፈታት እንችላለን ?

በአገር ቤት እነ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም፣ በዉጭ አገር ደግሞ አንዳንድ የፖለቲካ ደርጅቶች እንደሚሉት፣ ከምርጫዉ ደግሞ እራሳችን ብናገል ምን ጥቅም እናገኛለን? ወደ ምርጫዉ አለመግባታችን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ሊያስፈታ ይችላልን ?

ቁም ነገሩ ምርጫ መግባቱና አለመግባቱ ላይ አይደለም። እኛ አንድነትና ጥንካሬ ከሌለን ምርጫ ገባን አልገባን ምንም ለዉጥ አናመጣም። በመሆኑም ምርጫዉ እንደ ትልቅ ነገር ተደርጉ መታየት የለበትም ባይ ነኝ።

ገዢዉ ፓርቲ ስልጣን ከተቆናጠጠ አሥራ ስምንት አመት አለፎታል። (ደርግ በሥልጣን ላይ ከነበረበት ጊዜ የበለጠ) አንዳንዶቻችን ይህ የሆነበት ምክንያት ጠመንጃ ስላለዉ ነዉ እንላለን። አይደለም። ገዢዉ ፓርቲ በሥልጣን ላይ ያለዉ በተለያዩ መንገዶች ህዝቡንና ጠንካራ ተቃዋሚዎችን መከፋፈል በመቻሉ ነዉ።

አሁንም ከአሥር ወራት በኋላ ይደረጋል የሚባለዉ ምርጫ እየከፋፈለን እንደሆነ በግልጽ እየታየ ነዉ። «ብርቱክን ሚድቅሳ ካልተፈታች ምርጫ አንገባም ፣ ወይም እንገባለን» እያለን የምንጨቃጨቅና የምንከፋፈል ከሆነ፣ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ መታሰር እስከ አሁን እንደነበረዉ የአንድነታችን ምክንያት መሆኑ ይቀርና የመለያየታችን ምክንያት እየሆነ በመምጣት ላይ እንዳለ እናያለን። እኔ እንደማምነዉ ወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳ የታሰረችዉ ለዚህ አልነበረም።

ገዚዉ ፓርቲም እርሷን በግፍ አስሮ እርሷ ካልተፈታች «ምርጫ እንግባ፣ አንግባ» የሚል ግጭት በተቃዋሚዎች ዉስጥ በቀላሉ መዝራት ከቻለ፣ ገዢዉ ፓርቲ እርሷን የሚፈታበት ምንም ምክንያት አይኖረዉም። የርሷ መታሰር አሁን እንዳለዉ ተቃዋሚዎችን የሚስነጣጥቅ ከሆነ፣ ምን ቸገረዉና፣ እርስ በርስ እያጋጨ ስልጣኑን ያራዝማል እንጂ፣ ብርቱካን ሚደቅሳን ይፈታታል። ደግሜ እጠይቃለሁ **በዚህ ሁኔታ ወያኔ/ኢሕአዴግ ለምንድን ነዉ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን የሚፈታት ?**

ስለዚህ ከአሥር ወራት በኋላ በሚደረገዉ ምርጫ ዙሪያ አሁን እየተደረገ ያለዉ ክርክር ትግሉን የሚጠቅም ክርክር ሳይሆን ትግሉን የሚጎዳ፣ የምንወዳትና የምናከበራት የወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳ የቃሊቲ አሰቃቂ ኑሮን የሚያራዝም፣ እንደ አይጋ ፎረም ያሉ አፍቃሪ አምባገነኖችን ጮቤ የሚያስረግጥና ያለ ምንም ጥርጥር ገዢዉን ፓርቲ የሚጠቅም ወቅታዊ ያልሆነ ክርክር ነዉ።

ስለሆነም ሁላችንም ቆም ብለን እንድናስብና መሰረታዊ የሆኑ ጥያቄዎችን ለራሳችን እንድንጠይቅ ያስፈልጋል።

ይህን ብዬ ወደፊት እንድንራመድ ይረዳን ዘንድ፣ ይጠቅማሉ የምላቸዉን የሚከተሉት ስምንት ሃሳቦች በአክብሮት አቀርባለሁ።

1. ምርጫዉ አሥር ወራት ይቀሩታል። በመድረክ ዉስጥ ያሉ ድርጅቶች እንዲሁም መኢአድ በምርጫ እንሳተፋለን ወይም አንሳተፍም የሚሉ አስተያየቶችን ከመስጠት ተቆጥበዉ፣ ምርጫዉ ፍትሃዊና ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን በጋራ እንዲሰሩ ያስፈልጋል። በምርጫዉ ወቅት ምርጫ ማድረግ የማይቻልበት ሁኔት መሆኑ ግንዛቤ

ላይ ከተደረሰ፣ ባለፈዉ የወረዳና የማሟያ ምርጫ እንዳደረጉት ሁሉ፣ ያኔ በጋራ እራሳቸዉን ከምርጫዉ ያገለላሉ። በምርጫዉ መሳተፍ ጥቅም ካለዉ ደግሞ በጋራ ወደ ምርጫዉ ይገባሉ። ይህንን ዉሳኔ በጊዜዉ እንዲወስኑ ለነርሱ እንተወላቸዉ።

2. በአገር ቤት የሚኖሩ ተቃዋሚዎች ለምርጫዉ ከአሁን ጀምሮ፣ ምርጫ እንደሚሳተፉ በመገመት መዘጋጀት፣ የምርጫ ስትራቴጂ ማዉጣት፣ ተወዳዳሪዎችን መመደብ፣ ህዝብን ማስተባበር ይኖርባቸዋል።

3. ከገዢዉ ፓርቲ ጋር የሚደረገዉ ድርድር መቋረጥ የለበትም። ምርጫዉን በተመለከተ እስከሆነ ድረስ ድርድሮችን መካፈሉ ችግሩ አይታየኝም። አላወቅንበትም እንጂ ገዢዉ ፓርቲ ድርድሩን በመኢአድና በመድረክ መካከል መከፋፈልን ለመፍጠር እየተጠቀመበት ነዉ። ስለዚህ በሚቀርቡ አጀንዳዎች ሁሉ ላይ መወያይት እስከተቻለ ድረስ፣ **ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔት መድረኩ ወደ ድርድሩ ገብቶ ከመኢአድ ጋር አብሮ መሥራት ይኖርበታል ባይ ነኝ።**

4. በኢንጂነር ኃይሉ ሻወል የሚመራዉ መኢአድ የመድረኩ አባል ድርጅት ሆኖ የሚሰራበት መንገድ መፈለግ ይኖርበታል። ይህም ካልተቻለ ደግሞ መድረኩና መኢአድ ከገዚዉ ፓርቲ ጋርም ሆነ ከአለም አቀፉ ማህበረሰብ ጋር በሚያደርጉት ዉይይት በጋር በመሰልፍ የጋራ አቋም ማሳየት ይኖርባቸዋል። በአገር ዉስጥም ሆነ ከአገር ዉጭ የምንኖር ኢትዮጵያውያን በዚህ ረገድ ፓርቲዎቹን ትልቅ ግፊት ማድረግ ይኖርብናል ብዬ አምናለሁ።

5. የአንድነት ፓርቲ፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያምን ጨምሮ በርካታ የድርጅቱ የምክር ቤት አባላትን ከፓርቲዉ አግዷል። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያምና አብረዋቸዉ ያሉ በአንድነት የሥራ አስፈጻሚዉ ኮሜቴ ላይ ቅሬታ ያቀረቡ ወገኖች፣ አልተሳሳቱም ባልልም፣ ከደርጅቱ መታገዳቸዉ ግን የአንድነት ፓርቲን ያዳከመና ጠቃሚ ያልሆነ ዉሳኔ ነዉ ባይ ነኝ። የተወሰደዉም ዉሳኔ ምን ያህል የድርጅቱን ሕግና ደንብ እንደጠበቀ በግልጽ የሚታወቅ ነገር የለም።

   እነ ፕሮፌሰር መስፍን፣ ያለዉን ችግር በዉይይት ለመፍታት ፍቃደኝነታቸዉን እንደገለጹ አዉራምባ ታይምስ ዘግቧል። በመሆኑም አሁን ያሉት የአንድነት ፓርቲ አመራር አባላት በሌሎች የድርጅቱ አመራር አባላት ላይ የወሰዱትን እርምጃ ቀልብሰዉ፣ በድርጅቱ ዉስጥ ያለዉን ችግር በዉይይታና በንግግር መፍታት የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻት ይኖርባቸዋል የሚል ጠንካራ እምነት አለኝ።

   የአንድነት ፓርቲ የስለጠነ ፖለቲካን የሚያራምድ ፓርቲ ነዉ። ችግሮችን በንግግር መፍታት ሊያቅተዉ አይገባም። የአንድነት ፓርቲ አመራር አባላት አብረዋቸዉ ፓርቲዉን ከመሰረቱና አብረዋቸዉ ብዙ መስዋእትነትን ከከፈሉ የአንድነት መሥራች ወገኖች ጋር አብረዉ መሥራትና ችግሮቻቸዉን በንግግር መፍታት ካልቻሉ፣ በመድረኩ ዉስጥ ካሉ ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ጋር በዘላቂነት አብረዉ

ይሰራሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነዉ። በጥቂቱ ያልታመነ በብዙ እንዴት ሊሾም ይችላል ? (በዚህ አጋጣሚ በአገር ዉስጥም ሆነ ከአገር ዉጭ ያሉ የአንድነት ደጋፊዎች ጭፍን ድጋፍ ለፓርቲዉ ከመስጠት ተቆጥበን ፓርቲዉ ለድርጅቱ የሚጠቅመዉን መንገድ እንዲከተል ከፍተኛ ግፊት ማድረግ ይኖርብናል። ፓርቲዉ የድርጅቱ የአመራር አባላቱ ብቻ አይደለም።)

6. አቶ አሥራት ጣሴ እንዳሉት ምርጫ በማሸነፍ ወ/ት ብርቱካንን እናስፈታለን የሚለዉ አባባል ተቀባይነት የሌለዉ አባባል ነዉ። ምርጫ ተደረገም ፣ አልተደረገም ይችን ታላቅና ጀግና ሴት ለማስፈታት፣ ከምርጫዉ ጋር ያልተገናኘ፣ ሕዝባዊ ንቅናቄዎችን ማጧጧፍ ያስፈልጋል። የዉጭ ዲፕሎማቶችን ከማነጋገር፣ አንድ በአባላት ብቻ የተደረገ ሰልፍ ከማድረግና በጽ/ቤት ዉስጥ በየወሩ ከሚደረግ የሻማ ማብራት ሥነ-ሥርዓት ዉጭ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳን ለማስፈታት ይሄ ነዉ የሚባል እንቅስቃሴ ሲደረግ አላየሁም። እዉነቱን እንነጋገር ህዝቡን እንደሚገባ አላንቀሳቀስነዉም።

   በዚህ ረገድ የአንድነት ፓርቲ ብቻ ሳይሆን የመድረክ አባል ደርጅቶች ሁሉ እንዲሁም በአቶ ኃይሉ ሻወል የሚመራዉ መኢአድ ትልቅ ትኩረት ሰጥተዉበት የተቀናጀ ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች መጀመር ይጠበቅባቸዋል። ወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳ የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበርና መሪ ብቻ አይደለችም። ወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳ የመኢአድ፣ የአንድነት፣ የአረና፣ የኦሕኮ ….መሪም ናት። **ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ ዳግማዊት ጣያቱ ብጡል፣ የሁላችንም መሪ ናት።**

7. በዉጭ አገር ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችና የፖለቲካ መድረኮች ምርጫዉን በተመለከተ በየጊዜዉ ከሚያወጡት መግለጫ እራሳቸዉን እንዲቆጥቡ ያስፈልጋል። በአገር ቤት ያሉ ወገኖቻችን ናቸዉ አፈና፣ ችግር ፣ እሥር እየገጣማቸዉ፣ እየታገሉ ያሉት። «ወደ ምርጫዉ መግባት ያስፈልጋል፣ አያስፈልግም» ለሚሉት ጥያቄዎች፣ በጊዜዉና በሰዓቱ እነርሱ እራሳቸዉ የሚወስኑት ይሆናል። አሁን ማንሳት የማያስፈልግንን ነጥብ እያነሳን አላስፈላጊ ጭቅጭቅና ትርምስ ከመፍጠርና፣ ለገዢዉ ፓርቲ መጠቀሚያ ከመሆን መቆጠብ ይኖርብናል። አንርሳዉ የገዢዉ ፓርቲ ጥንካሬ የኛ መከፋፈል ነዉ።

8. በኢትዮጵያ ያሉ ወገኖቻችን፣ አገዛዙ ፍጹም አምባገነንና ግትር ከመሆኑ የተነሳ የሕዝቡ ሰቆቃና ስቃይ እየጨመረ ከመጣ፣ የፊታችን ምርጫም እንኳን በ97 ወደ ነበረው አይነት ሊቃረብ ቀርቶ ፍጹም አፈና የበዛበት ከሆነ፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎችም እራሳቸዉን ከምርጫዉ ያገላሉ የሚል ግምት አለኝ።

   ተቃዋሚዎቹ እራሳቸዉን ከምርጫዉ ካገለሉ ደግሞ ገዢዉ ፓርቲ በፎርፌ ብቻዉን፣ ወይንም ከነአይለ ጫሚሶ ጋር ተወዳደሮ አሸነፍኩ ማለቱ አይቀርም። የዉጭ ኃይላትም አገዛዙ ጥቅማቸዉን እስከጠበቀ ድረስ ይቃወሙታል ብዬ እራሴን

አላሞኝም። በኢራን እንደታየዉ ከተቃወሙም ተቃዉሟቸዉ ለትንሽ ጊዜ ብቻ ነዉ የሚሆነዉ። ጥቂት ሳምንታት እንዳለፉም ዝም ማለታቸዉና ገዢዉ ፓርቲ በእርዳታ ማንበሽበሻቸዉ አይቀርም። የማታ ማት ባዶዎችንን ልንቀር ነዉ ማለት ነዉ።

ስለዚህ በዉጭ አገር ያለን ኢትዮጵያዉያን አሁን ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚደረገዉን ትግል ሙሉ ለሙሉ እየደገፍን፣ የሚደረገዉ ጥረት ተገቢዉን ወጤት ካላመጣ አማራጭ መንገዶችን (PLAN B) ከአሁኑ ማዘጋጀት ይኖርብናል።

ለዚህም እንዲረዳ በአስቸኳይ የኢትዮጵያን አንድነትና ሉዓላዊነት ለድርድር ያላቀረበ ትብብር መፈጠር ይኖርበታል ባይ ነኝ። ይህ ትብብር «ምርጫዉ ከተጨበረበረና አገዛዙ የዘረጋዉን አፈና ከቀጠለ፣ በኢትዮጵያ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምንም ማድረግ ካልቻሉ፣ እነ ወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳ ካልተፈቱ ምንድን ነዉ መደረግ ያለበት ?» ለሚለዉ አንገብጋቢ ጥያቄ አስቸኳይ ምላሽ የሚሰጥና ትግሉን ወደ ምዕራፍ ሁለት የሚወስድ ይሆናል።

እዚህ ላይ ትብብር እንፍጠር ስል «ትብብር እንፍጠር» እያን ለአመታት እናዉራ ማለቴ አይደለም። ዉጭ አገር ባሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ዘንድ ስንሰማ የከረምነዉ የእንተባበርን ጥሪ መስማት ያልሰለቸዉ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም። የምንፈልገዉ ሁላችንንም ያደከመን የ«ትብብር እናድርግ» ወሬ ሳይሆን ትብብሩን ነዉ።

ዉድ የአገሬ ልጆች፣

አገዛዙ ተከፋፈሉ ሲለን አሜን ብለን መከፋፈል ማቆም አለብን። በዘር መከፋፈል መቆም አለበት። ምርጫ እንገባ አንገባ የሚል መከፋፈል መቆም አለበት። ሰላምዊ ትግል ይጠቅማል አይጠቅም የሚል መከፋፈል መቆም አለበት። በግለሰቦች ተክለ ሰዉነት ምክንያት የተፈጠሩ መከፋፈሎች መቆም አለባቸዉ።

ሁላችንም የድርሻችንን እንሥራ። ሁላችንም በሌላዉ ሥራ ጣልቃ አንግባ። ሁላችንም ልዩነቶቻችንን እንደያዝን መስማማት በምንችለበት ጉዳዮች ላይ አብረን እንሰለፍ። ሌላዉን ከማጥቃትና ከመቃወም እኛ የሰራነዉን ሥራ በተግባርና በተጨባጭ እናሳይ። እኛ የድርሻችንን ሳንወጣ የሚሰሩ ሌሎችን አናጣጥል። ትላንት ያጠፉን ካለንም ዛሬ አስተዋጾ ማድረግ ስንችል፣ በትላንት ጥፋታችን እየተደጋገመ አንኮነን። በትንሹም በትልቁም ልዩነት ሲፈጠር ለክስና «ወያኔ ነዉ» ለማለት አንቸኩል። እርስ በርስ በቅንነት እንቀባበል። የበሰልንና የነገዉን የምናይ እንጂ ወደ ኋላ የምናስብ፣ ትላንት የሰራናቸዉን ስህተቶች እየደጋገምን የምንሰራ፣ የማንማር ሰዎች አንሁን !

እግዚአብሄር ሁላችንንም ይርዳን !